# የታመሰው ተቃዋሚ

ኃይሉ አበበ

09-23-14

አምስተኛው አገር አቀፍ ብሄራዊ ምርጫ ደረሰ፡፡ መስከረምን ሳንቆጥር ስምንት ወራት ብቻ ይቀሩታል፡፡ የተቃዋሚው ጎራ በሀገር ውስጥና በውጭ ያለው አክራሪ ፅንፈኛ ተቃዋሚ ሀሳቡ በሁለት ተከፍሏል፡፡ በምርጫው መሳተፍና አለመሳተፍ ፡፡ በሀገር ውስጥ ያለው ተቃዋሚ መስመሩም አመለካከቱም የተለያየና የተበታተነ ነው፡ ፡ መቶ ቦታ የረገጠ ሺህ ቦታ የሚዛብር፡፡

በብሔራዊ ደረጃ ነው የተቋቋምነው የሚሉትም እንደ ስማቸው መለያየት ችግራቸውም የበረታና ብዙ ነው፡፡ አንድነት ከመድረክ ከታገደ (ከወጣ) በኋላ በአብሮነት ሲያራምዳቸው የነበረው ገመድ ተበጥሷል፡፡ መድረክ የብሔር ብሄረሰቦች መብትን ያከበረ እውቅና የሰጠ አንድነት ነው ሊበረታታ የሚገባው ባይ ነው፡፡ አንድነት ደግሞ ከጎሳ ተኮር ፖለቲካ ጨዋታ ወጥቶ በአንድነት ጉዳይ ላይ ብቻ ማተኮር አለብን ይላል፡፡

መድረክ አንድነት ፓርቲ ከስብስቡ አንዱ ሆኖ ሳለ ሌሎችን በሙሉ ልምራ፣ ልቆጣጠርና ልገምግም የሚል የበላይነት አቋም መያዙ ከሌሎች ጋር ሊያራምደው ስለማይቻል ራሱን መፈተሽ አለበት ይላል፡፡ በጀመሩት ሂደት የመግባቢያ ሰነድ ቢፈራረሙም አሁንም ፈተናና መሰናክል ገጥሞታል፡፡

የመኢአድን አመራር በፍርድ ቤት የከሰሱት እነ ማሙሸት አማረ አሁን ካለው የመኢአድ አመራር ጋር ሙግትና ግብግብ ገጥመዋል፡፡ በፍርድ ቤት ስለረታን አመራሩ ለእኛ ይገባል ነው የሚሉት፡፡ አመራሩ በበኩሉ በ97 ቅንጅትነት የታሰሩትን እነ ማሙሸትን በኢህአዴግ እየተረዱ ሊያፈርሱኝ እየተንቀሳቀሱ ሲል ይከሳል፡፡

በተቃውሞ ፖለቲካው ሜዳ ላይ ከእኔ ሌላ ማንም አንበሣ የለም የሚለው በፕሮፌሰር መሥፍን ወልደማርያም ከጀርባ የሚመራው በፊት ለፊት በኢንጂነር

ይልቃል ጌትነት አጋፋሪነት አክራሪና ፅንፈኛ የፖለቲካ መስመርን የሚያራምደው ሰማያዊ ፓርቲ ሁለት ዓመታት ብቻ ያስቆጠረ ቢሆንም የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሥልጣን ለመረከብ ዝግጁ ነን በቂ የተማረ የሰው ኃይል አለኝ እያለ ያላግጣል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ አዲስ ህገ መንግሥት ሰፊ እውቀትና ልምድ ባላቸው ታዋቂ ምሁራን አስጠንተን ተወያይተንበት አዘጋጅተናል፤ መንግሥት ለመምራት በሚያስችለን ጥሩ ቁመና ላይ እንገኛለን ሲል ይዛበታል፡፡

ሰማያዊ ፓርቲ ከአክራሪ እስላማዊ ኃይሎች ንቅናቄ ጋርም ቅንጅት ፈጥሮ በጠራው ሰልፍ አባላቱ እንዲገኙ እያደረገ አብሮ እየሰራ ሲሆን፤ አንዲት አባሉም በጁምዓ ሦላት ሁካታና ብጥብጥ ለመፍጠር ከሚሹ አክራሪዎች ጋር ተገኝታለች በሚል በቁጥጥር ሥር ውላለች፡፡ ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ እየታየ ነው፡፡ የሰማያዊና የአንድነት የተወሰኑ አመራሮችም ከግንቦት ሰባት ጋር ባላቸው ግንኙነት በህግ ቁጥጥር ሥር መዋላቸው ይታወቃል፡፡

በሰማያዊ ፓርቲ አባላት ውስጥ በተፈጠረው ከፍተኛ አለመግባባት ጠቅላላ ጉባዔ የሚጠራበት ወቅት ብዙ ስለተላለፈ ስብሰባ ይጠራ፤ አዲስ አመራር ይሰየም፤ ኢንጂነሩ በራሱ ጊዜ የሚንቀሳቀስ፣ ለፓርቲው ውሣኔ ተገዥ ያልሆነ ሰው ስለሆነ አመራሩን መልቀቅ አለበት የሚል የውስጥ እንቅስቃሴ እያካሄዱ ነው፡፡ አንዲት አባልንም ከሥራ አስፈፃሚነት አግደዋል፤ ሰላይ ናት በሚል፡፡ አቤቱታ ብታቀርብም ሰሚ አላገኘችም፡፡ሰማያዊ ፓርቲ የሚቃወመውን የጎጥ ፖለቲካም አራማጅ በመሆን የጎጃም ልጆችን  በአመራርና በቁልፍ ቦታዎች ማሰባሰቡም ኸረ ይኼ ነገር ወዴት እየሄደ ነው እያስባለው ነው፡፡

ይህ በአንድ ጎኑ እንዳለ ሆኖ የተቃዋሚው ጎራ ዛሬም ከትርምስ፣ ከውስጥ ትንቅንቅና ትግል እርስ በእርሱ ከመናቸፍና ከመናከስ አልወጣም፡፡ ስመ ብዙ ፓርቲዎች ድሮም  ነበሩ፤ ዛሬም አሉ፡፡ የተፈጠሩበት ኬሚስትሪ በውስጣቸው ያለው የአመለካከትና የአስተሳሰብ ወይንም የግንዛቤ ድህነት ጭርሱን እያራቆታቸው፤ ተማምለው እየተከዳዱ፤ አንድ ሆነው ተነስተው ሃምሣ ቦታ እየተከፋፈሉ፣ እየተሰነጠቁ፣ በስም እየተጣሉ እየተሟገቱ ይኸው ዛሬም ከጊዜ፣ ከዘመን መማር አቀበት ሆኖባቸው እንዳሉት አሉ፡፡ እንደሚኖሩትም ይኖራሉ፡፡

ያለማፈር አገርን ያህል ታላቅ ጉዳይ ሕዝብን የመሰለ ወሣኝ ኃይል እንመራለን ሲሉ ይህንን ማፈሪያ ማንነታቸውን ይዘው ሕዝቡን ከመናቅ የሚያደርጉትም ይመስላል፡፡ ወዲያ ማዶ በሀገረ አሜሪካ ያሉት ደግሞ ሰበር ዜና ብለው ከሰሞኑ ሦስት በትጥቅ ትግል ላይ ነን የሚሉ የጋራ ስምምነት ተፈራርመናል ብለዋል፡፡ አርበኞች ግንባር፣ የአማራው ንቅናቄና ግንቦት ሰባት መሆናቸው ነው፡፡

ይህንን ወደኋላ ላይ እንመለስበታለን፡፡ ኢትዮጵያ የሁሉም የጋራ አገርና ቤት እንደመሆኗ መጠን ስመ ብዙ ፓርቲዎች በቅድሚያ ማሰብ ያለባቸው አገሪቷ አሁን ያለችበትን ተጨባጭ እውነት፣ ልማትና እድገት በዓይናቸው የሚያዩትን የሚጨበጠውን ሥራ እንደሌለ አድርገው ከመካድና ከመሸምጠጥ መውጣት አለባቸው፡፡

ማንም መጣ ማንም ሄደ ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ በመለወጥ የተሻለች አገር በማድረግ በብዙ ፈርጆች አስደናቂ የልማትና የእድገት ሥር ነቀል ለውጥ በማምጣት የሰራውና እየሰራ ያለው ሥራ ከዚህ በፊት የነበሩት የተሻለ እድልና አጋጣሚ የነበራቸው መንግሥታት ያልሰሩት፣ ያልሞከሩትና ያላሰቡት ነው፡፡

ይህንን ለኢትዮጵያ ታላቅ ክብር፤ ቀጣዩም ትውልድ የሚኮራበትና በተጀመረው ላይ የሚቀጥልበትን ድንቅ ሥራ ለመከወን የበቃ በመሆኑ ሊመሰገን እንጂ የጥላቻ ፈረስ ጋላቢዎች ሊከሱትና ሊያጣጥሉት አይገባቸውም ነበር፡፡ ምክንያቱም እነዚህን ለአገር ተዓምራዊ ለውጥ ያስገኙ ሥራዎችን የተከለው በመላዋ ኢትዮጵያ ውስጥ በመሆኑ የትም ይዞት አይሄድምና፡፡

ፍፁም መንግሥትና መንግሥታዊ አስተዳደር በምድር ላይ የለምና የጎደሉ፣ የታዩ ክፍተቶችና ችግሮች እንዲታረሙና እንዲስተካከሉ መፍትሄ በጋራ እንዲመጣ የመፍትሄውም አካል በመሆን የሚሰራ ተቃዋሚ ሳይሆን አገሪቷ ያፈራችው በሌሎች አገራት ተቃዋሚም ዓይን ሲታዩና ሲመዘኑ፤ ኋላ ቀር የፖለቲካ ግንዛቤ ያላቸው ነው፡፡

በከፋ ጥላቻና በበቀል ስሜት የተዋጠ፣ በእብሪትና ከእኔ በላይ ለአገር አሳቢ የለም ብሎ የሚያክላላ፣ የሰለጠነ የውይይት፣ የፖለቲካ ባህል የሌለው፣ ልዩነትን የማያከብርና በጠላትነት የሚፈርጅ፣ በኃይልና በጉልበት የሚያምን፣ እርስ በእርሱ

እየተባላ፣ እየተጠፋፋና እየተናረተ ዛሬም ድረስ የቀጠለ፣ እንኳን አገር ለመምራት የራሱን ስመ ብዙ ፓርቲ በቅጡ መምራት ያልቻለ በተራ ምቀኝነት፣ በተራ ተንኮልና ሴራ፣በመንደር አሉባልታና ወሬ የተጠመደ እንኳን አገር ሊመራ ለራሱም የማይሆን ከንቱ ስብስብ መሆኑ ነው፡፡

የኢትዮጵያ ተቃዋሚዎች በጥቅሉ ከቀድሞ እስካሁን በዘለቀው ታሪካቸው ከአገርና ከወገን ፍቅር በላይ በራሳቸው ግላዊ ፍቅርና ራስ ወዳድነት የታጀሉ፤ አንዱ ሌላውን በንቀትና በበታችነትስሜት የሚያይ፤ እኔ የምለው ወይንም የማስበው ብቻ ነው ትክክል፣ የሌላው አመለካከትም ሆነ አስተሳሰብ ውዳቂ ነው ብለው የሚያስቡ፤ ሌላው ይህን ማሰቡም አማራጭ መፍትሄ ሳይሆን ጠላትነት ነው ብለው የሚፈርጁ፣ የሚወነጅሉ መግባባትም ሆነ መስማማት የሚባል ነገር ትናንትም ያልነበራቸው፣ ወደፊትም የማይኖራቸው ዓይነታቸው ግጥም የሌለው ነው፡፡ የትናንቱም፣ የዛሬውም፣ የወደፊቱም መፍትሄ ያላገኙለት የማያገኙለት የውድቀታቸውም ታላቁ መንስዔ ይኸው ነው፡፡

ሌላው ዓይነትና መለያ ባህሪያቸው ስለዴሞክራሲ፣ ስለ ሀሳብ ልዩነት፣ ስለ ግለሰብ መብት፣ ስለ መፃፍና መናገር ነፃነት፣ በተሸሞነሞነ ቃላት ቢናገሩም አንድ ሺህ አንድ ጊዜ ቢደጋግሙትም በተግባር ፍጹም ፀረ ዴሞክራሲዎች፣ ፍፁም አምባገነኖች እነሱን የሚተች፣ የሚቃወም፣ የሚነቅፍ ከእነሱ የተለየ ሀሳብ ያለውን እያሳደዱ አሥር ስም እየሰጡ፣ ስም እያጠፉ በህይወትም ጭምር ከማጥፋት የማይመለሱ መሆናቸው ነው፡፡

ከዚህ አንፃር ሲመዘን የቱንም ያህል ችግሮች ቢኖርበትም ኢሕአዴግ በኢትዮጵያ ታሪክ ከተከሰቱት የትናንትም የዛሬም ስመ ብዙ ፓርቲዎች ሁሉ ዴሞክራሲያዊ፣ የግለሰብ መብትና ስብዕናን፣ የሀሳብ ልዩነትን፣ ሀሳብን በፅሁፍና በመናገር የመግለፅ መብትን አቅሙ በፈቀደ ያስከበረና ያከበረ፤ ሰፊ ቻይነትና ትዕግስት ያለው ፓርቲ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የፖለቲካ  በትረ ሥልጣኑ በተቃዋሚዎች እጅ ቢሆን ኖሮ ዳግም ራሱ ተቃዋሚ ፕሬስም ሆነ የመፃፍ፣ የመናገር መብት፣ የሀሳብ ልዩነት፣ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር

ለአንድ ቀንም በኢትዮጵያ ህልውና አይኖርም፡፡ በፍጹም አምባገነንነት ያጠፉታል፡ ፡የማያከራክረው ውስጣዊ ማንነታቸው በእውነትም ይኼ ነው፡፡

ኢንጅነር፣ ዶክተር፣ ፕሮፌሰር ወዘተ...ያለው ሆኖ ቢሰባሰብም የማንነት መሠረቱ በእብሪትና በጀብደኝነት ከእኔ በላይ ማንም ለአገር አሳቢ የለም በሚል የአምባገነናዊ አስተሳሰብና እምነት ከመሠረቱ ጀምሮ የተገነባና በዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ያልተገራ፣ ያልተኮተኮተ ያልታነፀ በመሆኑ በሕዝባዊ አስተሳሰብና ከበሬታ በእኩልነትና ልዩነትን አቻችሎና ተቀብሎ ለጋራ አገር በጋራ የሚበጀውን በመሥራት ላይ የማያምን ለሕዝብ ፍላጎት ራሱን ያላስገዛ ነው፡፡ ለችግሩም መፍትሂ የማያመጣ በምሁርነት ስም ራሱን ከጣሪያ በላይ ኮፍሶ ልምራህ፣ ላስተዳድርህ፣ ለእኔ ብቻ መገዛት አለብህ፣ በእኔ አምልክ የሚል የፊውዳልና የቡርዣ ምሁራን ንቀትና ትዕቢት ኢትዮጵያን በመሰለ አገር ፋይዳም ተቀባይነትም የለውም፡፡

ሕዝባዊ ፍቅርና አስተሳሰብ በተግባርም የሕዝቡን ችግሮች በመረዳት ቀርቦ መፍትሂ መስጠት፣ ኑሮውን መኖር፣ ህይወቱን መካፈል፣ ከድህነት የሚወጣበትን፣ የሚሻሻልበትን የራሱን የቤተሰቡ ህይወት የሚለወጥበትን፣ ከተረጂነት ወጥቶ ራሱን የሚችልበትን፤ ትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ ንፁህ ውኃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የመንገድ አገልግሎት፣ የስልክና የብዙ አገልግሎቶች ተጠቃሚ የሚሆንበትን ታች ወርዶ፣ ሩቅ መንደርና ገጠር ተጉዞ የመሥራትን ቁርጠኝነት ይጠይቃል እንጂ ምሁር ነኝ፤ ከአሜሪካም ሆነ ከአውሮፓ መጥቼ ልምራህ ላስተዳድርህ ማለት ሳይማር ያስተማረን ሕዝብ መናቅና መድፈር ነው፡፡

በቅድሚያ በድህነት እየኖረ ያለውን እያካፈለ እሱ ሳይማር ያስተማረን፣ ከአፈር ታግሎ እያረሰ፣ ሳይለብስ ያለበሰን፣ ጫማ ሳያደርግ ጫማ ያጫማን፣ እንጨትና ኩበት ሸጣ፣ በወታደርነት በየበረሀው ዞሮ ተንከራቶ ግንባሩን ሰጥቶ ህይወቱን ከፍሎ አገር ያስረከበን፣ በትንሽ የመንግሥት ደመወዝ ያለውን እያካፈለ አስተምሮ ለቁም ነገር ያበቃን ቤተሰብ፣ ከጨለማ ወደ ብርሀን የመራችን ያስተማረችን ውለታና ወሮታ ልክፈላት፤ አገሬን ላገልግላት ሩቅ ነው ገጠር ነው መንገድ የለም መብራት የለም ሳልል በተሰጠኝ ሥራ የበኩሌን ብሄራዊ ግዴታዬን ልወጣ፣ ልለውጣት፣ ላሳድጋት የሚል ምሁር ዛሬ በአብዛኛው የለም፡፡

ከድህነት ላውጣት ከተፈጥሮ ሀብቷ እንድትጠቀምና እንድትበለፅግ እስከ መጨረሻው አቅሚና እስትንፋሴ ልስራላት፣ ትናንት ዝቅ ብሎ ሰርቶ አገሩን የሚለውጥና የሚያሳድግ ሳይሆን በእውቀቱ የሚኮራ፣ ለበለጠ ጥቅም ፍለጋ ደሀ አገሩን ጥሎ ስደትን የሚመርጥ በአገሩ የሚንቀውንና የማይሞክረውን ሥራ በሰው አገር እየሰራ የሚኖርና በዚህም የሚኩራራ፣ ደሀ አገር ያፈራችው ምሁርም አገሩን ትቶ ስደት መርጦ በሌላ አገር በተቀማጠለ ኑሮና ህይወት ደመወዝ የሚኖር እውቀቱን ለአገሩ ሳይሆን ለባዕዳን ገብሮ የሚኖር ነው፡፡

በባዕድ አገር በእውቀት አንቱ ተብሎ ሲሰራ ለድሀ አገሩ አንዲት ስንዝር አስተዋጽኦ ያላደረገ ግና ደግሞ ሌላው ኢትዮጵያን ለመለወጥ ለማሳደግ ከድህነት ለማውጣት የሰራውን ታላቅ ሥራና የከፈለውን መስዋዕትነት የሚያጣጥል፣ የሚያናንቅ፣ የሚያንቋሽሽ፣ ፖለቲካ ሲባል ደግሞ ከየቢራ ቤቱ ተጠራርቶ ሲቃወም፣ ሲጮህ፣ የሚውል እኔ ነኝ ኢትዮጵያን መምራት ያለብኝ ብሎ የሚያውካካ የእናት እንባና እርግማንን የተሸከሙ ጉዶች ነው ኢትዮጵያ ያፈራችው፡፡ እዚያም በስደት ሆነው በሰው አገር ተነጋግረው የማይግባቡ፣ ጎራ ለይተው የሚዘናጠሉ፣ አገር ቤት ያለውም ተቃዋሚ በቦክስ፣ በድንጋይና በዱላ፣ እርስ በእርስ የሚናረቱ፣ የሚባሉ፣ ከጎዳና ጎረምሳ የቡጢ አስተሳሰብ ያልወጡ፣ ኑሯቸው አሉባልታ፣ ስም አጥፊነት፣ የመንደር ወሬና መንደርተኛነት የተጣባቸው እብሪተኛ፣ አምባገነን፣ ጻተኛ ተቃዋሚዎችን ነው አገሪቷ ያፈራችው፡፡

በሀሳብ ልዩነት ተካረው ቡጢና ቦክስ ድንጋይና ዱላ የተማዘዙ በእጃቸው መሣሪያ ቢኖር ደግሞ ይጨራረሳሉ፡፡ እንግዲህ እነዚህ ናቸው ኢትዮጵያን ካልመራን ሞተን እንገኛለን እያሉ የሚያውካኩ ተቃዋሚዎች፡፡ ሕዝብ አላበደም እነዚህን ሀገር ይመራሉ ያስተዳራሉ ብሎ የሚመርጠው፡፡ሀገር መጫወቻ መቀለጃ አይደለችም፡፡

እነዚህ ቡድኖች፣ ስብስቦች፣ ድርጅቶችና ፓርቲዎች መሪዎቻቸውም እነሱም ከጥላቻ ከእብሪት፣ ከጀብደኝነት፣ ከስሜታዊነት፣ ከጠላትነት፣ ከመፈራረጅና ከመጠፋፋት፣ አንዱ ሌላውን ከመናቅና ተገቢ ክብር ካለመስጠት፣ የሀሳብን ልዩነትና ዴሞክራሲን ከመርገጥ ከስም አጥፊነትና ከተመፃዳቂነት፣ የቆሸሸ አገርና ትውልድ ገዳይ ከሆነው መድኃኒት ከሌለው በሽታቸው ሊወጡና ሊፈወሱ እስካልቻሉ ድረስ ኢትዮጵያን እንመራለን፣ እናስተዳድራለን ብለው ባያስቡ ባይመኙም ይመከራሉ፡፡

ራሳቸውን በቅጡ መምራት ያልቻሉ አንድ ሆነው ተነስተው መቶ ቦታ የሚሰነጣጠቁ በክህደት የሚወነጃጀሉ፣ በመበላላት የሚያምኑ፣ በእብሪትና በንቀት የተሞሉ ሥነ ሥርዓት፣ ሥነ ምግባር፣ ባህልና ጨዋነት ብሎ ጭራሹንም የማያውቁና ያልፈጠረባቸው በቂም በቀልና በደም ጥማት ናላቸው የዞረ አክራሪ ተቃዋሚዎች መቼም ሆነ መቼም አስተዋዩንና ጨዋውን የኢትዮጵያ ሕዝብ አይመሩትም ፡፡

ከእባብ እንቁላል እርግብ አይጠበቅም እንዲሉ አገሪቷን የሌላ ዙር የደም መፋሰስ ማዕከል ለማድረግ፣ አንድ ተተኪ አዲስ ትውልድን በጥላቻና በበቀል በመመረዝ እንዲጠፋፉ ለሚሰሩ ኃይሎች ኢትዮጵያና ሕዝቧ ቦታና ሥፍራ የላቸውም፡፡ ማሰባቸውም በራሱ ይገርማል፡፡ እንኳን ወደ አመራር ሊመጡ ይቅርና ሕዝብ ከእንደነዚህ ዓይነት ተቃዋሚዎች የሚጠብቀው ተስፋ የሚያገኘው ትሩፋት የለውም፡ ፡ በልጆቹ በሠላሙ፣ በአገሩ ልማትና እድገትም አይደራደርም፡፡

ከሻዕቢያ ጋር ሆነው ከጀርባ የሚያሴሩና የሚመክሩ ማፈሪያዎች ኢትዮጵያን እንመራለን ብለው ለመመኘት የሞራልም የስብዕናም ብቃቱ የላቸውም፡፡ እዚያው በጠበላችሁ - አሜሪካና አውሮፓ ላይ እየተሰለፋችሁ፣ መፈክር እያሰማችሁ፣ ሲያሻችሁም መፈክር ፅፋችሁ እያወጣችሁ፣ እድሜ ከሰጣችሁም የዛሬ 20 እና 30 ዓመት ከዚያም በላይ መኖር ትችላላችሁ፡፡ ኢትዮጵያ በሠላም ውላ በማደር፣ ሰርታም በመለወጥ በማደግ ወደተሻለም እድገት በመገስገስ ላይ ያለች አገር በመሆኗ የእናንተን ሁከት፣ የትርምስ፣ የአመፅ ጫጫታ ለመስማት ጊዜ የላትም - አትሰማችሁም፡፡

ወደፊት…ወደፊት እናት አገሬ ማሪኝ ብላችሁ የምትመጡበት፣ ሕዝቧን ይቅርታ የምትጠይቁበት፣ መስሎን ነበር የምትሉበት ጊዜ ሩቅ አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ እናንተ ከምታውቋት በላይ ተለውጣለች፡፡ ስለማታውቋት ኢትዮጵያም ከማውራት ተቆጠቡ፡፡

እናንተ ብዙ ዓመታት በወሬ፣ በጥላቻ፣ በቀውስ ተጠምዳችሁ ድንጋይ እየነከሳችሁ ስትወራጩ፣ መንግሥትና ሕዝብ ደግሞ ሌት ተቀን በሥራ ተጠምዶ ከድህነትና ከተረጂነት ለመውጣት የሰራው ታላቅ ተግባር ፍሬ አፍርቷል፡፡ እናንተም

የማያባራውን ለከት የሌለውን ወሬና አሉባልታችሁን ቀጥሉ፤ በሐፍረት ትዋረዱበታላችሁ፡፡ ኢትዮጵያና ልጆቿም በአሸናፊነት ይገሰግሳሉ፡፡